ከገበሩ አድጋቦ ሕዳር 12/2000

ሊዎን / ፈረንሳይ

# “ዝምታ ለበግም አልበጃት

# አስራ-ሁለት ሁና አንድ ነብር ፈጃት!”

ኣረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ..ሕ.ኢ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሂጃችሁም ወይኔ!።

ዝምታችን ተናቀ

ግራሞታችን ጠለቀ

የዕምነት-ቃል-ኪዳን ተሰረቀ

ምንደኛ በገድሌ ተሳለቀ

ወዳጅ ከህሊናው ተላቀቀ

የሳቡት ቃታ ባረቀ

በቃ! በቃ! አለቀ፤ደቀቀ።

“የማይሆን ፀሎት፤ለቅስፈት”

ያንን የደም-ማዕበል. . .

ግዝፈቱን፤ ክበደቱን ረሱት

የተመተረዉን ስጋ. . .

. . .የተከሰከሰዉን አጥንት

የቃ-ቃ ጨዋታ አረጉት?

ያለ ቃሉ ሲያውሉት

ሲድሩበት፤ሲዳሩበት!

ጥቁር ጥላሸት ሲኩሉት

እንዲህ ያለዉን ሽፍጥ. . .

. . . ለ እምዬ ምን ልበላት?

ነው እንዴ የልጇ ሞት?

ርካሽ-ሞት፤የውሻ ሞት?

ኣረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ.ሕ.አ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሄጃችሁም ወይኔ!

አንድ ልጁ በቀትር

በፋሺስት፤ጥይት ዐረር

ደሙ ሲፈስ፤ሲንዠረዠር

ስጋው ሲከተፍ፤ሲመተር

የወላድ ቤት፤ሲበረበር

በውጪ-ግቢ ነፍስ ሲታደር

በሌት በቀን ሲደፈር

የተቆመለት፤ከትር

የሰማዕታት ደብር

ያኖረውን ክብር።

ምን መስሎአቸዋልሳ!

እነነሲቡ! በየፓልቶኩ ነገሩነ

ኢ.ሕ.አ.ፓን፤ይዘን ወጣነ!

አወይ የጉድ አገር!

ቆጠሩት እንዴ  የዐረብ ሽቀጥ?

በገንዘብ፤በሶልዲ የሚሸቀጥ፤

ወይስ የሞፈር ዕንጨት፤የማገዶ ፍልጥ፤

ከሞኝ ገበሬ ደጃፍ ፤የሚቆረጥ

ወይስ የፋብሪካ አቶሞቢል

በቁልፍ የሚንቀሳቀስ. . .

ቆርቆሮ፤የሚንከባለል

ወይስ የተዝካር ድግስ

ለነበስ-ይማር የሚዳርስ

ወይስ መገበያያ-ዘንቢል?

ተነስቶ የሚንጠለጠል

ወይስ ቤት ማሳመሪያ

የዕራስጌ ጌዮ አደረጉት

ወይስ የጎረቤት ድሰት

ሲቸግር የሚዋሱት

ወይስ የቻይና ሻንጣ

ይዞ ሮጦ የሚወጣ

ወይ ጣጣ! ፈጠጣ

ሰማዕት ረገጣ

የማያዘልቅ ደፈጣ

ገበጣ፤ገበጥባጣ

የሞኝ ለበጣ።

<u>እኔስ ቋንቋ አጣሁለት</u>

<u>ለንዲህ ዓይነቱ ቅዠት</u>

<u>የቁም ዕብደት</u>

<u>የቁም ሞት</u>

አረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ..ሕ.አ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሂጃችሁም ወይኔ!

ለካስ ታሪክ ራሱን ይደግማል?

ባንድነት ያዳግማል?

ክህደት ያገረሻል?

የ"ሀ" እና የ"ለ" በሂል

ወልደ-ብርሀነ-መስቀል!

የጌታቸው ማሩ ፍልፈል!

ዘመም-ዘንበል፤ወለል-ወለል

የነጩ ቤት ባለሙአል

የነጭ-ግርፍ፤ጀንፈል

በጋሻው-ዝበሃል

የ"ብተና" ኮሶ-ትል

አጉራ-ዘለል

ጥዶ ዘለል።

ኣረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ..ሕ.አ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሂጃችሁም ወይኔ!

ወይ አለመመልከት! አለማስተዋል!

በሬ ካራጁ ሲውል!!

በ አትላንታው መደብል

ከዝግና እልፍኝ ገብቶ ሲዶል

በዕምነት ብንቀላቀል

ቢቸረው ዳግም ዕድል

ቃኤል-ጌታቸው-ቃኤል

መጥለፊያውን፤ሲገምድ-ሲፈትል

ዕቡያን ቦድነዋል?

ነዳያን አድብተዋል?

ካራዉን ሲሞርድ፤ሲስል

መርሻንም ሲያነሆልል

የሆዱን በሆዱ ይዟል

ባጭር ጊዜ፤ባመት-ተኩል

ተላላወን ሲያባብል

ሲፈነቅል፤ሊያስፈነቅል

ሲ-ያ-ብ-ል፤ሲ-ያ-ብ-ል፤ሲያብል!

ዕቡያን ቦድነዋል?

ነዳያን አድብተዋል?

አረም አብቅሎ ኑሯል?

እንደልቡ ሊንደባለል

ጥራዝም ተነጥቋል

አዲስ ዘፈን ወጥቷል

"የአክ-ሊሉ" ምርኮ

"ስታትስኮ!፤ምንትስኮ!"

ክህደት ማሳመሪያ ቡልኮ።

ኣረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ..ሕ.አ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሂጃችሁም ወይኔ!

ዶሮ ብታልም ጥሬዋን

አለማወቅ አቅምዋን

ያፌንጫ-ያፌንጫዋን፤

የስር፤የስር-ስርዋን

መደየን! መኮነን!

አወይ ጉድ! ወይ ቅዠት!

የአንጃነት እዠት

ጥጋብ ወይስ ንቀት?

ምን የሚሉት ዕብደት

ልክን የነሳ ቅብጠት

እንዲህ ዓይን ማውጣት

ከድፍረትም፤ድፍረት

ኣረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ.ሕ.አ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሂጃችሁም ወይኔ!

በወንድሜ በአጥንቱ

መጣቹ፤በስሙ፤በሃውልቱ

ምትክ በሌለው ንብረቱ

በ አንድዬ ምልክቱ

የማይሆን-ቧልት፤ገልቱ!

ኣረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ..ሕ.አ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሂጃችሁም ወይኔ!

የበሰበሰ ዘናብ አይፈራም

ባዶ-ሽጎዬ፤ገም-አይፈራም

መሬት-ከፍ፤ሰማይ-ዝቅ ቢል

አለና በደም የተፃፈ ውል

ክቡር ታሪክ፤የጀግና ገድል

የመሬትን-ስበት፤የቀይሯል?

ዉሃን፤ሽቅብ ያፈሷል?

የማይቻለውን መከጀል

ዓርማ-ክታቤን መከጀል

መጃጃል! መጃጃል! መጃጃል!።

ኣረ እዘያው በዐጥቢያችሁ

ኢ.ሕ.አ.ፓ ዕንደሁ ለእኔ

የዓይኔ ብሌን ነው የዓይኔ

ለድፍረታችሁ መጥኔ!

ለመሂጃችሁም ወይኔ!

ቀይ በርቷል እዚያው ቁሙ!

ጠፍቶአችሁአል ነገር-ዓለሙ

ለ ዕድራችሁ ስም ሰይሙ

"የሌባ ዓይነ ደረቅ"

ኢ.ሕ.አ.ፓ.ን ለቀቅ፤አንጅነትን ጠበቅ!

ቸር ይግጠመን